MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND

# 2ኛ ክፍለጊዜ የውጤት መስጫ ለ2ኛ ክፍል የወላጆች መመሪያ

በማርክ መስጫ 2 ወቅት፣ የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለጸው ፅንሰሀሳቦችና ክህሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።
እባክዎ ልብ ይበሉ፦ በ *በኢታሊክስ* የታዩት ጽንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ትምህርት ተሰጥቶባቸዋል ነገር ግን በሪፖርት ካርዱ ላይ ደረጃ/ዉጤት አልተገለጸም።

## ሒሳብ

### መለካት እና የተመዘገበ መረጃ

- በአንድ የቁጥር መስመር ስዕል ላይ ከ 0 በመጀመር ሙሉ ቁጥሮችን ከቁጥር 0፣ 1፣ 2 ጋር በሚዛመዱ እኩል የቦታ ርቀቶች ያላቸዉ ነጥቦች እና በቁጥር መስመር ላይ በ 100 ውስጥ የሙሉ ቁጥር ድምርን እና ልዩነቶችን መወከል/ማሳየት።
- በ$ እና ¢ ምልክቶች በኣግባቡ በመጠቀም፣ የዶላር ወረቀቶች/bills፣ ሩብ ብሮች/quarters፣ ኣስር ሳንቲሞች/dimes፣ ኣምስት ሳንቲሞች/nickels እና አንድ ሳንቲሞች/ፔኒዎች የሚያካትቱ የቃል ፕሮብሌሞች መፍታት። ለምሳሌ፦ 2 ዳይም እና 3 ፔኒዎች ካላችሁ፣ ስንት ሳንቲሞች ኣላችሁ?

### ቁጥሮችና ግብረቶች በኣስሮሽ ቤት

- በ1000 ውስጥ መቁጠር፤ በ5ቶች፣ በ10ሮች፣ እና በ100 እየዘለሉ መቁጠር።
- በቦታ ዋጋ፣ በግብረቶች ባህርያት፣ እና/ወይም በመደመር እና በመቀነስ መካከል ባለው ግንኙነት በተመሰረቱ ስልቶች በመጠቀም፣ በ100 ውስጥ በቅልጥፍና መደመርና መቀነስ።
- በቦታ ዋጋ እና በግብረቶች ባህርያት በመጠቀም፣ የመደመርና የመቀነስ ስልቶች ለምን እንደሚሰሩ ማብራራት።

### ስሌቶች እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን በቅልጥፍና መደመር እና መቀነስ።
- ከ20 ቁጥር በታች በሚከተሉት ስልቶች በመጠቀም መደመር እና መቀነስ
  - o በመቁጠር፤
  - o በዚህ መልክ አስር በማድረግ(ምሳሌ፣8+6=8+2+4=10+4=14)፤
  - o ወደ ኣስር የሚመራ ቁጥርን መበተን (ለምሳሌ፦13-4=13-3-1=10-1=9)፤
  - o በመደመር እና በመቀነስ መካከል ባለው ግንኙነት በመጠቀም (ለምሳሌ፣ 8+4= 12 እንደሚሆን በማወቅ፣ 12-8= 4) እንደሚሆንም ይታወቃል፤
  - o ተመጣጣኝ ነገር ግን ቀላል ወይም የሚታወቅ ድምር መፍጠር (ለምሳሌ፦ 6 + 7 በመደመር የሚታወቀውን ተመጣጣኝ መፍጠር 6+6+1=12+1=13)።
- መቁጠርን ከመደመር እና መቀነስ ጋር ማዛመድ (ለምሳሌ፣ 2 ለመደመር 2 ላይ መቁጠር)።
- በሁሉም ቦታዎች ያልታወቁ ያሉበት በ20 ውስጥ መደመርና መቀነስን በመጠቀም የማከል፣ የመቀነስ፣ ኣንድ ላይ ማሰባሰብ፣ መበተን፣ እና የማወዳደር ሁኔታዎችን የሚያካትቱ የቃል ፕሮብሌሞችን መፍታት።(እስከ 20) ስብስብ እቃዎች ውስጥ ጎደሎ ቁጥር እና ሙሉ ቁጥር ያላቸውን መወሰን ለምሳሌ፣ እቃዎችን በማጣመድ ወይም ሁለት በሁለት በመቁጠር፤ የሁለት  እኩል ቁጥሮች ድምሮች ሙሉ ቁጥር መሆኑን ለማሳየት ቀመር መጻፍ።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፦ ስነ ፅሁፍ

- በፅሁፍ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ዝርዝሮችን መረዳትን ለማሳየት ማን፣ ምን፣ ዬት፣ መቼ፣ ለምን፣ እና እንዴት የመሳሰሉ ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ።
- ተረቶች እና ኣፋዊ ስንፅሁፎች ከተለያዩ ባህሎችን የሚያካትቱ ታሪኮች እንደገና ማውራት፣ እና ማእከላዊ መልእክት፣ ትምህርት፣ ወይም ግብረገባቸውን መወሰን።
- በአንድ ትረካ ላይ ያሉ ገፀ-ባህርያት ለኣይነተኛ ክውነቶች እና ፈተናዎች እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ መግለፅ።
- በገጸባሕርያት መካከል የኣስተያየቶች ልዩነቶችን ማወቅ፣ በከፍተኛ ድምፅ ንግግርን ሲያነቡ ለያንዳንዱ ገፀባህርይ በተለየ ድምፅ መናገርን ጨምሮ።
- ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የተለያዩ የኣንድ ታሪክ ትርጉሞች (ለምሳሌ፦ የሲንደሬላ ታሪኮች) በተለያዩ ደራሲያን የተደረሱ ወይም ከተለያዩ ባህሎች የመነጩ ማወዳደርና ማነፃፀር።
- የኣንድ ታሪክን ኣጠቃላይ መዋቅር መግለፅ፣ መጀመርያው ታሪኩን እንዴት እንደሚያስተዋውቅ እና መጨረሻውም ተግባሩን እንዴት እንደሚያጠቃልለው በማካተት።
- በሁለተኛ ክፍል ደረጃ በአግባቡ ውስብስብ የሆነ ስነ-ጽሑፍን አንብቦ በትክክል የመረዳት ችሎታ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፦ መረጃዊ

- ማን፣ ምን፣ ዬት፣ መቼ፣ ለምን፣ እና እንዴት የሚሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅና በመመለስ በፅሁፍ/ምንባብ ላይ ያሉ ቁልፍ ዝርዝር መረዳትን ማረጋገጥ።
- የባለ-በርካታ-ኣንቀፅ ጽሁፍን ዋና ርእስ እንዲሁም በፅሁፉ ውስጥ የተለዩ ኣንቀፆች ትኩረትን መለየት።
- ለ2ኛ ክፍል ርእስ ወይም የርእስ መስክ ኣስፈላጊ የሆነ ፅሁፍ ውስጥ የሚገኙ ቃላት እና ሃረጎች ትርጉም መወሰን።
- የተለያዩ የጽሑፍ ገጽታዎችን በመጠቀም(ለምሳሌ፦ የምስል መግለጫ፣ ጉልህ ጽሁፍ፣ ንኡስ ርእሶችን፣ የቃላት መፍቻ፣ ኤሌክትሮኒክ ምልክቶችና፣ ተምሳሌት ምልክቶችን) ዋነኞቹን እውነታዎች በፅሁፍ ውስጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ ማግኘት።
- የተለዩ ምስሎች (ለምሳሌ፦ ማሽን እንዴት እንደሚሰራ የሚያሳይ ንድፍ) ኣንድን ፅሁፍ ለማብራራት እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ማብራራት።
- ለ2ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆኑ መረጃያዊ ፅሁፎችን ማንበብ እና መገንዘብ።

### ቋንቋ፦ የቃላት ዝርዝር ግኝት እና አጠቃቀም

- ስለ ሁለተኛ ክፍል ርእሶች እና ፅሁፎች በኣነስተኛና በትላልቅ ቡድኖች ውስጥ ከእኩዮችና ኣዋቂዎች ጋር ከተለያዩ ሽርኮች ጋር በሚካሄዱ የትብብሮች ዉይይት ውስጥ መሳተፍ።
- ከጽሑፍ ከፍ ባለ ድምጽ ከተነበበ ምንባብ፣ ወይም በቃል የተነገረ ወይም ከሌላ ሚድያ ቁልፍ ሃሳቦችን በመውሰድ በዝርዝር መናገር/ማስረዳት።
- በአንድ ተናጋሪ የተነገረ ሃሳብን በተናጋሪው/ዋ በኩል ምን እንደተባለ መረዳትን ለመግለጽ፣ተጨማሪ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ወይም ስለ ርዕሱ ወይም ጉዳዩ በጥልቀት ለመረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅ እና መመለስ።
- ያልታወቁ ወይም በርካታ ትርጉም ያላቸውን ቃላት እና ዓረፍተነገሮች ለ2ኛ ክፍል ምንባብ ይዘት ከተደረደሩት ስልቶችን በመለዋወጥና በመምረጥ ትርጉማቸውን መግለጽ።

## ጽሑፍ

### ትምህርት ሰጭ/ገላጭ

- በውስጣቸው ኣንድን ርእስ የሚያስተዋውቁ መረጃያዊ/ገላጭ ፅሁፎችን መፃፍ፣ እናም ነጥቦችን ለማዳበር በሃቆችና በፍቺዎች መጠቀም።
- የመደምደምያውን ሃሳብ ወይም ክፍል ግለጽ/ግለጪ።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- በአዋቂ/ትልልቅ ሰዎች እና እኩያሞች ጋር በመመራትና በመታገዝ በርዕሱ ላይ በማተኮር ክለሳ በማድረግ ኃሳብ መቃኘት እና እንደ አስፈላጊነቱ መጻፍን ማጠናከር።
- ከኣዋቂዎችና ከእኩያዎች ኣመራርና ድጋፍ ጋር፣ ፅሁፍን ለማፍለቅና ለማተም በተለያዩ ዲጂታል መሳርያዎች መገልገል፣ ከእኩያዎች ጋር መተባበርንም ጨምሮ።
- በየጋርዮሽ ምርምርና የፅህፈት ፕሮጀክቶች መሳተፍ (ለምሳሌ፣ ኣንድ ዘገባ ለማፍለቅ በኣንድ ርእስ በርካታ መፃህፍትን ማንበብ፤ የሳይንስ ትዝብቶችን መመዝገብ)።
- ከልምድ/ገጠመኝ የተገኘ መረጃ በማስታወስ/በመጥቀስ ወይም ከተሰጡ ምንጮች መረጃ በመሰብሰብ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት።

### የቋንቋ አጠቃቀም

- የታሪኮችና የግጥሞች ኣውዲዮ ቅጂ መፍጠር፤ ተገቢ ሲሆን ኣስተያየቶችን፣ ሃሳቦችን፣ እና ስሜቶችን ለማብራራት፣ በሚታወሱ ተሞክሮዎች ወይም ታሪኮች ላይ ስእሎችን ወይም ሌሎች የሚታዩ ትርእይቶች መጨመር።
- የተጠየቀ ዝርዝርን ወይም ማብራርያ ለማቅረብ፣ ለትግባሬና ለሁኔታ ተገቢ ሲሆን፣ ሙሉ ኣረፍተነገሮችን ማፍለቅ።
- ከባለቤቱ ጋር በሚጣቀስ ተውላጠስም መጠቀም (ለምሳሌ፣ እኔውራሴ፣ እኛውራሳችን)።

- ኣዘውትረው የሚታዩ ኢልምዳዊ ግሶች ያለፈውን ጊዜ አመልካችነታቸዉን መቀየስ/መፍጠር እና ኣግልግሎት ላይ ማዋል (ለምሳሌ፣ sat, hid, told)።
- ቅጽል እና ተወሳከግስ በመጠቀም ገላጭነታቸው ስም ወይም ግስ ከሆነ ከሁለቱ መምረጥ።
- ሃሳብን በማፍለቅ፣ በማስፋት፣ እና በማስተካከል የተሟላ የነጠላ እና ድርብርብ አረፍተነገሮች መስራት (ለምሳሌ:- ልጁ ፊልም ተመለከተ፣ ትንሹ ልጅ ፊልም ተመለከተ፣ የድርጊቱ ፊልም በትንሹ ልጅ ታይቷል)።
- በፅሁፍ የመደበኛ እንግሊዝኛ በትልቅ ፊደል ኣጠቃቀም/capitalization፣ በስርአተ ነጥብ እና በስፔሊንግ ደንቦች በቂ ችሎታ ማሳየት።
- በአፃፃፍ፣ ኣነጋገር፣ በምንባብ፣ ወይም በማዳመጥ በቋንቋ እውቀት እና በህጎቹ መጠቀም።

### ትረካ

- ከሚያቀርቡት/ከሚነገረው በሰፊው የተብራራ ክስተት ወይም አጫጭር ክስተቶች ትረካ ጻፍ።
- ትግባሬዎችን፣ ሃሳቦችን፣ እና ስሜቶችን ለመግለፅ ዝርዝሮች ማካተት።
- የክስተት/የክውነት ቅደምተከተል ለማመልከት በጊዜያዊ/በኣለማዊ ቃላት መጠቀም።
- የመዝጊያ መልእክት ስጥ/ስጪ።

## ሳይንስ

### መሬትና የህዋ ሳይንሶች

- በአንድ አካባቢ የሚገኝ ውኃ ቅርጹን እና የመሬት አቀማመጡን የሚያሳይ ሞዴል/ናሙና ስራ/ሪ።
- በመሬት ላይ ውኃ የት እንደሚገኝ እና ጠጣር ወይም ፈሳሽ ሊሆን እንደሚችል በመለየት መረጃ/ኢንፎርሜሽን አግኝ/ኚ።
- የመሬት ክውነቶች በፈጣን ወይም ዘገምተኛ በሆነ ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል መረጃ ለመስጠት ከተለያዩ ምንጮች መረጃ/ኢንፎርሜሽን ተጠቀም/ሚ።

### ኢንጂነሪንግ ንድፍ እና ሂደት

- አንድን ችግር ለመፍታት የአንድ ቁሳዊ ነገር በሚፈለገው አይነት መሥራት እንዲችል ቅርጽ እንዴት እንደሚረዳ ለማስረዳት ቀላል ንድፍ፣ ስዕል፣ ወይም አካላዊ ሞዴል አዘጋጅ/ጂ።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ጂኦግራፊ

- ምድር ላይ ያሉ ቦታዎችን ለማግኘትና ለመግለፅ በጂዮግራፊካዊ መሳርያዎች መገልገል።
- በኣንድ ኣከባቢ ውስጥ ቦታዎችንና ክልሎችን በጂዮግራፊካዊ ገፅባህርያት በመጠቀም መመደብ።
- ሰዎች ለኣካባቢያቸው እንዴት እንደሚሻሻሉ፣ እንደሚከላከሉ፣ እና እንደሚለወጡ ማብራራት።

### ባህል

- የሁለት የተለያዩ ባህሎች ንጥረነገሮች እና እያንዳንዳቸው ሰብአዊ ፍላጎታቸውን እንዴት እንደሚያሟላ እና ለማህበረሰቡ ኣስተዋፅኦ እንደሚያደርግ መተንተን።
- የተለያዩ ግለሰቦችና ቡድኖች ኣንድ ማህበረሰብ ለመገንባት ከሌሎች ባህሎች እንደሚጋሩና እንደሚዋሱ ማብራራት፡

## መረጃዊ/ኢንፎርሜሽናል ማንበብ እና መጻፍ

- ልቦለድ እና ልቦለድ ያልሆነ ስነጽሑፍ ከእውነታ ጋር ያለውን ግንኙነት መለየት።
- የመረጃን ፍላጎት ለማሟላት ጥያቄዎችን ማዘጋጀትና ማሻሻል።
- ተፈላጊ መረጃ ለማሟላት መገልገያዎችን መለየት።
- የመረጃ ፍላጎትን ለማሟላት ምንጮችን ማግኘትና መምረጥ።
- መረጃዎች ለማግኘት በተለዩ ምንጮች መገልገል።
- ውሂብ/መረጃ በተለያየ ቅርፀት መቅረፅ/መመዝገብ።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።
- የተፈላጊ መረጃን ግኝቶች/መደምደሚያዎች ለማጋራት ለማዘጋጀት በተለያዩ ቅርፀቶች መጠቀም።

## እደጥበብ

### የሥነጥበብ ፈጠራ እና ከሥነጥበብ ጋር ያለ ግንኙነት

- ለአንድ የፈጠራ ፕሮብሌም ምላሽ ለመስጠት የተለያዩ አቀራረቦችን በመለየት ተግባር ላይ አውል/ይ።
- ስለ ማህበረሰብ አስተሳሰቦችን የሚወክል የእደጥበብ መሠረታዊ ነገሮችን እና የንድፍ መርሆችን ተጠቀም(ሚ)።
- የስነ ጥበብ መሳሪያዎች፣ ሚዲያ፣ እና የስራ ቦታን ሲጠቀሙ ተገቢውን ቅደም ተከተል/ሂደት ያሳዩ።
- ዝርዝሮችን በመጨመር እና የእጅ ሥራዎችን በማሳየት የስነጥበብ ስራን አሻሽል(ይ)።
- ስለ ቤት፣ ትምህርት ቤት፣ ወይም የማህበረሰብ ህይወት የሚገልጽ የሥነጥበብ ሥራ ፍጠር(ሪ)።
- ከተለያዩ ማህበረሰቦች የጥበብ ስራ ዓላማዎችን አወዳድር(ሪ)/አነፃፅር(ሪ)።

### የኪነጥበብ አቀራረብ እና የኪነጥበብ ግብረመልስ

- በማህበረሰብ ትርኢት/ኤግዚብሽን ላይ መሪ ሃሳብ/ገዢ ሃሳብን በመለየት የስነጥበብ ሥራው የተመረጠበትን አሳማኝ ምክንያት ግለጽ(ጪ)።
- ለእይታ የሚቀርብ የእደጥበብ ሥራ ለማዘጋጀት ልዩ ልዩ አይነት ቁሳቁሶችን እና ዘዴዎችን አወዳድር(ሪ)።
- በትምህርት ቤቶች ውስጥ እና ከትምህርት ቤቶች ውጭ ለእይታ የቀረበ/አውደ ርዕይ እደጥበብ ለማህበረሰብ ምን አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ገምግም(ሚ)።
- የሥነጥበብ ሥራን ስነጥበባዊ መለያ ባህርይ፣ ገላጭ ባህርይ ለመወሰን ምስልን በቃላት በመግለጽ ተንትን(ኚ)/ዘርዝር(ሪ)።
- ተመሣሣይ መልእክት/አገላለጽ ያላቸውን ምስሎች የፍሬ ነገሩን ፍቾ ትርጉም ለመስጠት አነፃፅር(ሪ)።
- የራስን የእደጥበብ ሥራ ውበት ለመገምገም የተዘጋጀ መስፈርት በመለየት ተግባራዊ አድርግ(ጊ)።

## ሙዚቃ

### የሙዚቃ ዝንባሌ/ምላሽ መስጠት

- ተነፃፃሪ እና ተደጋጋሚ ክፍሎችን የሚያካትት ሙዚቃ መጫወት።
- ሙዚቃ የማይጨምር-የማይቀንስ የድምፅ ምት/ድለቃ እየተዘመረ ወይም እየተሰማ በተለያየ ሚትርስ/meters መንቀሳቀስ።
- በዘፈን ግጥሚያዎች የእንቅስቃሴ ተከታታዮችን መጫወት።
- በሙዚቃ ቅንብሮችና ሌሎች የእውቀት መስኮች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች አስስ(ሺ)/መርምር(ሪ)።
- በተሰጡ መስፈርቶች በመጠቀም የመማርያ ክፍል ጨዋታ ኣቅርቦቶችን መገምገም።
- ለራሳቸው ወይም ለሌሎች አፈጻጸም አግባብ ያለዉ የታዳሚ ባህሪያት መስፈርቶችን መለየት።

### የሙዚቃ ፈጠራ

- ለመማሪያ ክፍል ውስጥ መሳሪያዎች ተገቢውን የመጫወቻ ዘዴ ማሳየት።
- የተሰጠን ዜማ ለማጀብ በቦርደን መጫወት።
- ከተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች እና ከኣለም ባህሎች፣ የተወሰኑ ከኣጠቃላይ የመማርያ ክፍል ጥናቶች ጋር የተያያዙትን ጨምሮ፣ ዘፈኖችን/መዝሙሮችን እና ዳንሶችን ማቅረብ።

### የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት

- ቀላል የስንኝ፣ እና የድምፅ ቃና/ጥርቀት፣ ሐረጎችን እና ምልክቶችን ማንበብ።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

**የጤንነትና- አካላዊ ብቃት እንቅስቃሴ**

- የደም ማሰራጫ ስርአት ክፍሎች ለጂምናስቲክ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ መለየትና ማሳየት።
- የሰውነት አካል ለጂምናስቲኮች ምላሽ ለምን እንደሚሰጥ መለየት (የልብ ምት፣ እስትንፋስ፣ ላብ)።
- ከጤና ጋር የተያያዙ ብቃቶችን ለማራመድ፣ የጡንቻ ጥንካሬ፣ እስትንፋስ-ነክ ችሎት/የልብ ማስተንፈስ ዘላቂነት/aerobic capacity/cardiorespiratory endurance፣ እና ተጣጣፊነት/flexibilityን በሚያካትቱ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ።
- በአመጋገብ እና በአካል ማጠንከርያ መካከል ግንኙነት መለየት።
- በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ወቅት የተለዩ የልብ ትርታ ነጥቦችን መዳሰስ/መፈለግ።
- የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በልብ ትርታ ላይ እንዴት ተፅእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት።

**የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች**

- በተለያዩ እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ፣ ግለሰቦች እንዴት በተለያዩ የፍጥነት መጠኖች በየደረጃዉ እንደሚገሰግሱ እውቅና መስጠት።
- የአንድ ሰው ችሎታ/እውቀት እድገት ውጤት ከባለፈው ልምድ፣ የተፈጥሮ ችሎታ፣ እና የልምምድ ውጤት የሚመነጭ መሆኑን መገንዘብ።
- ከጊዜ ወደጊዜ ከልምድ የተነሳ ጥበብ፣ ችሎታ፣ ሙያ፣ እንደሚዳብር መገንዘብ።
- አዎንታዊ/መልካም አስተያየት በክዋኔ/አፈጻጸም ላይ አስፈላጊነቱን መገንዘብ።
- በስተላይ-የተወረወረን ነገር መያዝ ማሳየት።
- በመያዝ፣ መግፋት፣ እና መወርወር ላይ የሚያስፈልጉ ክሂሎቶችን ማጣራት።

## የጤና ትምህርት

**የተፈጥሮ አካል እና የተጠቃሚ ጤንነት Physical and Consumer Health (PCH)**

- የግል ጤንነትን የማሻሻል ወይም የመንከባከብ መንገድ ማብራራት።
- በማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የጤና አገልግሎቶችን መለየት።
- በብክላ የተፈጠሩ የጤና ጉዳዮችን መለየት።

**Safety and Injury/ደህንነትና ጉዳት (SI)**

- ለአስቸኳይ ሁኔታዎች በአግባቡ ምላሽ የመስጠት ችሎታን ማሳየት።
- ከቤት ውጭ በደህንነት የሚቆይባቸው መንገዶችን መለየት።
- ከማያውቋቸው ሰዎች/ከባይተዋሮች በደህንነት ለመጠበቅ ተግባሮችን መለየት።
- በተለመዱ ሰዎች አካባቢ በደህንነት የመቆያ ተግባሮችን መግለፅ።